መርፌ ሌሎች ስለታማ መሣሪያዎችን ማስወገድ ይኖርብሃል፡፡ ያለበለዚያም በእንፋሎት ኃይል መቀቀል ይኖርባቸዋል፡፡

*******

## ገቢር ሁለት

**የበሽታዎች ጠቅላላ ስብሰባ**

ማማዱ ማኪ ባሕ፣ እድሜ 17፣ ማሊ እና የእርሱ ቡድንን ሃሳብን መሠረት ያደረገ

አቅራቢ (ለካሜራ)

ላለፉት 100 ዓመታት በሽታንና ሕመምን በመዋጋት ብዙ መሻሻሎችና አድርገናል፡፡ ነገር ግን በቅርቡ የተከሰተው አዲስ በሽታ ብዙ ስቃይን አስከትሏል፡፡ ይህም በሽታ ኤድስ ይባላል፡፡

-

- እስከ አሁን ምንም መዳኛም ሆነ ክትባት የለውም ነገር ግን ራሳችንን ለመከላከል በጣም ቀላል እና ውጤት ያለው እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ ይህም በተረት የምትሰማው እና አሁን እየነገርኩህ ያለው ነው፡፡ ይህም በማይደረስበት ትንሽ ዓለም፣ ለዓይን በማይታይ በአጉሊ መነጽር ብቻ በሚታይ እና በበሽታዎች ዓለም የሚገኝ ነው፡፡

(በትረካ የሚቀርብ)

በዚህ በሽታዎች ባሉበት ዓለም ልክ እንደ ሰው ምድርና በሽታዎች በሚኖሩበት ከተማ ወይም መንደር አለ በተለይም በሽታዎች እንዲኖሩ የሚያስችል ጀርም አለ፡፡

(በትረካ የሚቀርብ)

እንደ አባል ጓደኞቼ! ኮንታሚኖል ተብሎ በሚታወቅ መንደር ነው የሚኖረው፡፡ የመንደሩም ኃላፊ ኃይለኛ ከሚባለው የቲቢ ቤተሰብ መካከል ይገኛል፡፡

ቲቢ (ማንባ ነቀርሳ)

- ተመልከት ነጭ የደም ሴል!
- አቅራቢ - በዛ መንደር ብዙ ቤተሰቦች አሉ እነርሱም የልጅነት ልምሻዎች፣ የኩፍኞች፣ የወባዎች፣ የጉበት በሽታዎች እንዲሁም የአባላዘር በሽታዎች ለምሳሌም ቂጥኝና ጨብጥ በእርግጥም የተቅማጥ በሽታዎች ቤተሰብ ይኖራል

- ተቅማጥ - በኮንታሚኖስ ያለፉት ዓመታት ገደቢስ እና አስደንጋጭ የሆነ ነበር
- ሁላችን የተቀደስን ነን። በግልጽ ከሚታወቁት ቤተሰቦቻችን አንዱ ፊንጣጣ ከምድረ-ገጽ ጠፍቷል። የክትባት መገኘት የበሽታዎችን መኖር እንደ ፖሊዮ ለመሣሰሉት አስፈሪ ነው።

አቅራቢ - (በትረካ የሚቀርብ) ነገር ግን አንድ ቀን እንግዳ ዋናውን ኃላፊ ለማነጋገር መጥቶ ነበር።

(በትረካ የሚቀርብ) እንግዳውና ዋና ቲቢ (የሣንባ ህመም) ሌሊቱን በሙሉ ሲወያዩ ነበር

- ተቅማጥ - የኮንታሚኖስ መልካም ሕዝቦች እንኳን በደህና መጣችሁ! ይቅርታና!
- አዎ! ጨካኝነቱ ከታላላቅ በሽታዎች መካከል እንዲሆን ካደረገው ቲቢ (ሣንባ ነቀርሳ) ግዛት እንኳን በደህና መጣችሁ!
- ቲቢ (ሣንባ ነቀርሳ) - የኮንታሚኖስ ሕዝቦች <<በሽታ ከራሳችሁ ጋር ይሁን!>>
- ሕዝቡ - በሽታ ካንተም ጋር ይሁን!
- ቲቢ (ሣንባ ነቀርሳ) - እዚህ የተሰበሰብነው ስለሚያበሳጨው የሰው ልጆች ፕሮጀክት ጉዳይ ነው። ይውደሙ! ምክንያቱም በእኛ ላይ እውነተኛ የሆነ ጦርነት ከፍተዋል።
- ሰዎቹ በጤና ዘመቻቸው እኛን ለማጥፋት አቅደዋል።
- ጥቂቶች - (ተስፋ አስቆራጭ ነገር) ለዚሁ ነው የተዘጋጀነው
- ቲቢ (ሣንባ ነቀርሳ) - ነገር ግን አትፍሩ። የስቃያችሁ ማብቂያው ቀርቧል
- ይኸው አለን! በሽታዎችን ለመንከባከብ እና ለሰው ልጆች መውደቅ ከእኛ ጋር ሁኑ የተከበሩ አስፈሪ፣ የጌቶች የበላይ የሆኑ አጥፊ የበሽታዎች መሪ ኤድስ
- ሕዝቡ (ያጨበጭባል)
- ኤድስ - <<በሽታ ካንተ ጋር ይሁን!>> በቅርብህ ወዳለ ቦታ ልመጣ ነው። የኔ ኃይል ሰብአዊነት ስላስከተለብን ችግር ዋጋ ሊከፍል ይገባዋል።
- ፖሊዮ - የጌቶች ጌታ ኤድስ! ቃልህ ጥሩ እና መልካም ነው ነገር ግን አሁን የምንፈልገው ተግባር ነው። ያለው ሁኔታ ጥፋት ነው ከቤተሰቦቹ ጥቂት የሆኑ ሰለባዎች አሉ።
- ኤድስ - ጀርም ፖሊዮ! ያንተን ጭንቀት እና ትኩረት ተረድቻለሁ የመተላለፊያው መጨረሻ ቅርብ ነው። ላደርጋቸው ያቀድኩትን ላንተ ከማካፈሌ በፊት በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ወደዚህ መጥተው የእኔ ረዳት እንዲሆኑ እጋብዛቸዋለሁ።

- እናንተ እና እኔ መጥፎ ተግባራትን እየፈፀምን ያለን ጓደኞቼ!
- ይህን ያዙልኝ /እቃ ይሰጣቸዋል/
- ይህ በጣም አሪፍ የሆነው ሰዎችን የማጠቃበት ሥልት ነው ወደ ሰውነታቸው ውስጥ ልንገባ የምንችልበትን ዘዴ እንጀምር
- የደም ወይም የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን መንገድ ልንጠቀም እንችላለን በሦስተኛና በመጨረሻም ከእናት ወደ ልጅ ልንተላለፍ እንችላለን፡፡
- በደም የመተላለፊያው መንገድ በቫይረሱ ከተያዘው ወደ ጤነኛው ሰው ሲሆን ስለታማ በሆኑ ነገሮች እንደ ምላጭ፣ መርፌ እና ቢላዋም ይተላለፋል፡፡
- እና የወባ ጀርም ምን ይመስልሃል?
- ወባ - ጌታው ኤድስ! ጓደኛዬ የሆነችው ትንኝ የሰው ልጅ በማስያዙ በኩል ልትረዳህ ትችላለች::
- ኤድስ - ጀርም ወባ አትኩሮትህን አደንቃለሁ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በወባ ትንኝ አማካይነት የኤድስ ቫይረስ ሊተላለፍበት አይችልም::
- ስለዚህም መተላለፊያው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ነው:: የሰው ልጅ ልቅ የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽም እኔ ያዝኩት ማለት ሲሆን ለእኔ ሁሉንም ለማመቻቸት ሌሎች ተጨማሪ በሽታዎች እንደ አባለዘር በሽታዎች በማስያዝ ይቀልልኛል፡፡
- የጉበት በሽታ - አነጋገርህ ለስላሳ ነው. . . ወሬ. . . ወሬ. . . ከተናገርከው ውስጥ በእውነት ምንም አዲስ ነገር የለም:: አንዱ በሰው ሰውነት ውስጥ ከገባህ ምንድነው የምትፈጽመው::
    - ኤድስ - በጠቅላላው የሚገርምህ ለሰው ልጅ የመከላከያ ኃይል ዘዴ ምሥጋና ይግባውና በዚህ ብቻ ሊቆይ ይችላል::
    - ለምሳሌም፡ በደም ውስጥ የሚራወጡ ያንተን እህትና ወንድም ጀርሞችን የሚገድል ነጭ የደም ሴል ማለቴ ነው::
- የእነዚህ ነጭ የደም ሴሎች መደምሰስ ለእኔ ብልጽግና ነው:: አንዴ እነዚህን ካጠፋኋቸው የሰው ልጆች ለተለያዩ በሽታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ::
- ማንባ ነቀርሳ (ቲቢ) - አዎ ይህ የመከላከያ ዘዴ አስፈሪ ደረጃ ላይ ደረሰ ማለት ነው

- ኤድስ - ይህን ተከትለህ በዚህ መካከል በሰላም ራስህን አረጋግተህ በአጭር ወይም በረጅም ጊዜ ሞቱን ማምጣት ብቻ ነው:: ሰዎች ኤድስ ሌላውን ሰው ሰለባ አደረገው ይላሉ ነገር ግን አሸናፊው አንተ ራስህ ነህ::
- የጉበት በሽታ - ጌታው ኤድስ! ለመሆኑ እኔ ጎበዝ ፍጡር ነኝ ብሎ ራሱን የሚገምት ሰው ሊያስቆምህ የሚችልበት መንገድ የለውም?
- ኤድስ - አዎ በእርግጥ እኔን ማስወገጃ ብቸኛ መንገድ መከላከል ብቻ ነው
- ሕዝቦቼ - መከላከል?
- ኤድስ - ሰዎች ቀድሞ ጥቅም ላይ የዋለን ወይም ከጀርም ነጻ ያልሆኑ ስለታማ ነገሮችን መጠቀም የለባቸውም!
    - ወሲብ የሚፈጽሙም ከሆኑ ለአንድ ሰው ታማኝ ሆነው አለበለዚያም ኮንዶም መጠቀም አለባቸው
- የአባለዘር በሽታዎች - ገዳዩ መግሪያ!ገዳዩ መግሪያ!
- ኤድስ - በእኔና በአንተ ይቅርና የሰው ልጆች ይህንን ቀላል ሕጎችን ይከተላሉ ብለህ ታስባለህ?
- ሁሉም በአንድ ላይ - አይከተሉም! አይከተሉም!
- ማንባ ነቀርሳ (ቲቢ) - የኮንታሚኖስ ሕዝብ! ዛሬ ይኼ መከላከያ መንገድ ከተነገረው መንደራችንን ያስለቅቀናል
- ኤድስ - ደህና! ውድ ጓደኞቼ ሁላችሁም ዝግጁ ሁኑ፡፡ የተቅማጥ ጀርም ይጠራችሁና እናሸንፋቸዋለን፡፡
    - አሁን መሄድ አለብኝ በርቱና ሥሩ፡፡

አቅራቢ - አዎ በተካሄደው ስብሰባ ስለ በሽታዎች ጠቃሚ ነገሮችን እኔም አንተም አግኝተናል፡፡ ስለዚህም እንዴት የኤድስ ቫይረስን መከላከል እንደሚቻል እንዳወቃችሁ ተስፋ አደርጋለሁ:: ይህን መረጃ በአካባቢያችሁ ላሉት ለጓደኞቻችሁ ለቤተሰቦቻችሁ አካፍሉ ኤድስን መከላከል ያስችላቸዋልና በአንድ ላይ ሆነን ለኤድስ ወረርሽኝ ግብአተ መሬቱን እንፈጽምለታለን፡፡

ማነው በጣም ጎበዝ ? እኛ ወይስ ኤድስ ?

/በመጋረጃው ላይ አንድ ቃል ይታያል/ ኤድስን እንቅደመው!

*******